# የ2022 ሜሞሪያል ቀን ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

የሕይወትን ዛፍ መብላት፣ ማለትም፣ ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን መደሰት
በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ዋናው ጉዳይ መሆን አለበት።

በዘፍጥረት 2፡9 ያሉት ሁለት ዛፎች—
የሕይወት ዛፍ እና የክፉና መልካም የሚያስታውቀው ዛፍ—
ሁለት መርሆችን ይወክላሉ—
የሕይወትን መርህ እና የትክክል እና የስሕተት መርህ።

የጌታ ምለሳ ጌታ ኢየሱስን በቀደመው ፍቅር፣
በምርጡ ፍቅር የመውደድ ምለሳ እና
እንደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ
ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መገንባት ለሆነው
ለሕይወታዊው የክርስቶስ አካል ግንባታ
ጌታ ኢየሱስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመብላት ምለሳ ነው።

የሕይወት ዛፍ እንደሆነው እንደ የክርስቶስ ርቢ፣
በክርስቶስ ያመንን እና የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን እኛ፣
የዘላለም ሕይወት ያለን እና የዘላለምን ሕይወት መለማመድ የምንችል ብቻ ሳንሆን
ይህንን ሕይወት ለሌሎች የክርስቶስ አካል ብልቶች ማገልገልም እንችላለን።

*© 2022 Living Stream Ministry*

## መግቢያ፡-
## ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ የመደሰትን መንገድ መከተል

### ከወንድም ሊ ወሳኝ የሆነ ኅብረት

“የሕይወት ዛፍ ለሰው ሕይወት የሚያካፍለውን፣ እና ሰውን ደስ የሚያሰኘውንና የሚያረካውን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል”—“*Life Study of Genesis*” ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 141 የተወሰደ።

“የሚያስፈልገን አንዱ ነገር ጌታን እንደ ሕይወት ዛፍ መደሰት ነው”—“*The Tree of Life*” ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 23 የተወሰደ።

“በግንቦት 1935 ዓ.ም. (እ.አ.አ) ከባድ የሆነ የቲቢ በሽታ ይዞኝ ነበር...በታመምኩበት የሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ የሕይወትን ዛፍ አየሁ። በእነዚያ ሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ በጌታ ምለሳ ውስጥ እና በሥራው ውስጥ ሕይወት እንዳልነበረን አየሁ። የትኛውም ችግር ቢሆን፣ እያንዳንዱ ዓይነት ችግር የሕይወት እጥረት ውጤት ነው። ይህን ሳይ እጅጉን ተጸጸትኩ፣ ብዙ ተናዘዝኩ፣ በጌታም ፊት ጥልቅ-ዝርዝር ንስሐ ገባሁ፣ በእርሱም ፊት ብዙ ማስተካከያዎችን ከእርሱ ተቀበልኩኝ...የሕይወትን ዛፍ የሚመለከቱት መልእክቶች ብዙ ቅዱሳንን አዳኑ፣ በናንኪንግ ያሉት ብዙ ወንድሞችና እኅቶችም በመልእክቶቹ ተለቀቁ። በሻንጋይ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ለአራት ዓመታት በቆየው የቤተ ክርስቲያን ነውጥ ቅዱሳን ተስፋ ቆርጠውና በጭንቀት ውስጥ ነበሩ፣ ምንም ነገር ማድረግም አልቻሉም ነበር። እነዚህ መልእክቶች መንፈሳቸውን ለቀቁት፣ ልባቸውንም በአብርሆት ሞላው...ስለ ሕይወት ዛፍ በተሰጡት መልእክቶች አማካኝነት በሻንጋይ የነበረችው  ቤተ ክርስቲያን ስለተፈወሰች ጌታን አመሰግነዋለሁ...ስለ ሕይወት ዛፍ የተነገሩት መልእክቶች በሻንጋይ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን መነቃቃት መሠረትን መሠረቱ”—*The History and Revelation of the Lord's Recovery, vol.1*፣ ከገጽ 130፣ 133፣ 135፣ 138።

“የሕይወትን ዛፍ መብላት፣ ማለትም፣ ክርስቶስን እንደ ሕይወት አቅርቦታችን መደሰት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋናው ጉዳይ መሆን አለበት”—ከሪካቨሪው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ራእይ 2፡7፣ ከ6ኛው የግርጌ ማስታወሻ፣ ከአራተኛው አንቀጽ የተወሰደ።

“የክፉ ሰዎች ክፉው ሁኔታቸው ጌታን ለመመገብ እና ለመደሰት ወደ ጌታ አለመምጣታቸው ነው...ብዙ ነገሮችን ያደርጋሉ፣ ነገር ግን ከጌታ ጋር ለመገናኘት፣ እርሱን ለመውሰድ፣ እርሱን ለመቀበል፣ እርሱን ለመቅመስ እና እርሱን ለመደሰት ወደ ጌታ አይመጡም። በእግዚአብሔር እይታ ከዚህ የሚበልጥ ክፉ ነገር የለም”—ከሪካቨሪው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ኢሳ. 57፡20፣ የግርጌ ማስታወሻ 1።

እግዚአብሔር ለሰው ያለው ውጥን፣ ሰው እርሱን ይደሰተው ዘንድ ለሰው  እንደ ሕይወት ዛፍ ራሱን መስጠት ነበር። “እግዚአብሔር እርሱን እንደሰተው ዘንድ እንደሚፈልግ እና ለእርሱ ምንም ነገር እናደርግ ዘንድ እንደማይፈልግ ማየታችን፣ የክርስቲያን ሕይወት ሁሉ የድሰታ ጉዳይ እንደሆነ ማየት ነው...እነዚህን ሁለት ነጥቦች እናይ ዘንድ ጽንሰ-ሃሳባችን ከተለወጠ፣ እግዚአብሔርን የመደሰት ሕይወት መኖር ቀላል ይሆንልናል”—“*The Vision of the Tree of Life and the Tree of Knowledge of Good and Evil*” ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 60 የተወሰደ።

“እግዚአብሔርን የመደሰት መንገድ መከተል ከፈለግን የጽንሰ-ሃሳብ ለውጥ ሊኖረን ይገባል...እግዚአብሔርን ወደ መደሰት እውነታ ውስጥ መግባት ከፈለግን፣ የሚቆጣጠረንን ራእይ ማየት አለብን...የአርባ ዓመት ዕድሜ እስኪሞላኝ ድረስ እርሱን የምደሰትበት መንገድ አልተገለጠልኝም ነበር። ለሃያ ዓመታት አብዛኛው ጊዜዬና አቅሜ በመባከኑ አዝኜ ነበር። አብዛኞዎቹ ጸሎቶቼ ዋጋ አልነበራቸውም፣ መጽሐፍ ቅዱስን እና ሌሎች መንፈሳዊ መጽሐፍትን ለማንበብ ያጠፋሁት ጊዜም ምንም ዋጋ አልነበረውም። የምንሠራበት መንገድ እና የመንፈሳዊ ፍለጋችን መንገድ የተሳሳተ እንደነበር የተገነዘብኩት ያን ጊዜ ነበር...የተሳሳተ መንገድ በመውሰዴ ትልቅ ኪሳራ ስለደረሰብኝ፣ ሌሎችም ይህንን ስሕተት እንዲደግሙት አልፈልግም። ሌሎች እግዚአብሔርን የመደሰት መንገድ እንደሚከተሉ ተስፋ አደርጋለሁ። ቅዱሳን የተሳሳተ መንገድ እንዳይከተሉ እማጸናለሁ። የቀደመውን የፍለጋ መንገዳችንን ማሰብ አለብን። ከባድ የሆነ የጽንሰ-ሃሳብ ለውጥ ሊኖረን ይገባል። የሚቆጣጠር ራእይ ሊኖረን ያስፈልገናል”—“*The Vision of the Tree of Life and the Tree of the Knowledge of Good and Evil*” ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 51 የተወሰደ።

*© 2022 Living Stream Ministry*

**የሜሞሪያል ቀን ኮንፍረንስ አውትላይኖች**

**ግንቦት 19-21/ 2014**

**አጠቃላይ ርዕስ፦**

**ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመደሰት መንገድን መከተል**

መልእክት አንድ

**ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መፈጸም**

**ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ የመደሰት መንገድን መከተል**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 2፡7-9፤ ራእ. 2፡7፤ 22፡14፤ ዮሐ. 1፡4፤ 14፡6፤ 10፡10፤ 6፡35፣ 57፣ 63

I. **በዘፍጥረት 2 በሰው ፊት ሁለት አማራጮችን እናያለን—የሕይወት ዛፍ እና መልካምና ክፉን የሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ—ቁ. 7-9፦**

ሀ. ሁለቱ ዛፎች በዚህ አጽናፍ-ዓለም ሰው በነጻ ፈቃዱ እንዲመርጣቸው ሁለት ፈቃዶች፣ ሁለት ምንጮች፣ እና ሁለት አማራጮች እንዳሉ ያሳያሉ—ተዛ. ዘዳ. 30፡19-20።

ለ. የሕይወት ዛፍ፣ በዘላለም ኢኮኖሚው መሠረት የእግዚአብሔርን የመጀመሪያውን ውጥን በማሳካት ለሦስታንዱ አምላክ ክብር፣ ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ ሰው ይደሰተውና ይቀናበርበት ዘንድ በምግብ መልክ ለሰው እንደ ሕይወት የቀረበውን የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነውን ክርስቶስ ያሳያል—ዘፍ. 1፡26፤ ኢሳ. 43፡7፤ ዘፍ. 2፡9፤ ራእ. 2፡7፤ 22፡14፤ ዮሐ. 1፡4፤ 14፡6፤ 10፡10፤ 6፡35፣ 57፣ 63፤ ራእ. 21፡10-11፤ ተዛ. 4፡3፦

1. የሕይወት ዛፍ፣ የእግዚአብሔር ዛፍ፣ አምላክ-ዛፍ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ነው።
2. ብሉይ ኪዳን የሚጀምረው በሕይወት ዛፍ ነው (ዘፍ. 2፡9)፣ አዲስ ኪዳን የሚደመድመው በሕይወት ዛፍ ነው (ራእ. 22፤2፣ 14)፤ ስለዚህም፣ እግዚአብሔር ለሰው ሕይወት የመሆኑ ሃሳብ በመላው የመለኮታዊው መገለጥ ውስጥ የሚገኝ ነው።
3. እግዚአብሔር ሰውን ከሕይወት ዛፍ ፊት ለፊት ማስቀመጡ እግዚአብሔር የሰው ማንነት ቅንብር ይሆን ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን ሕይወታዊ በሆነ መንገድ በመመገብ እና ገንብ-አፍራሽ በሆነ ቅንባሮ ከራሱ ጋር በማዋሃድ እንደ ሕይወቱ እንዲወስደው እግዚአብሔር እንደፈለገ ያመለክታል—ዮሐ. 6፡57፣ 63፤ ኤር. 15፡16፤ ማቴ. 4፡4።

ሐ. መልካሙን እና ክፉን የሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ ለሰው የሞት ምንጭ የሆነውን ሰይጣንን ያመለክታል—ዕብ. 2፡14፦

1. መልካም ነገሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ነገሮች እና ኃይማኖታዊ የሆኑ ነገሮችንም ጨምሮ፣ እግዚአብሔር ራሱ ያልሆነ ማንኛውም ነገር ሞትን ወደ ሰው ለማምጣት በተንኮለኛው፣ በሰይጣን፣ ጥቅም ላይ ሊውሉ ስለሚችል መልካሙን እና ክፉን የሚያስታውቀው የእውቀት ዛፍ ከእግዚአብሔር ውጪ የሆኑ ሁሉንም ነገሮች ጨምሮ ያመለክታል—ዮሐ. 5፡39-40፤ 2 ቆሮ. 3፡6።
2. መልካም እና ክፉ የተመለከቱት በሁለት ዛፎች ሳይሆን በአንድ ዛፍ፣ በሁለተኛው ዛፍ ነው፤ ስለዚህም ከእግዚአብሔር ውጭ መልካም ነገርን መፈለግ ከሰይጣን ነው።
3. እውነተኛው መልካም እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ በመሆኑም፣ እግዚአብሔርን ማግኘት እውነተኛውን መልካም ከማግኘት ጋር እኩል ነው—ማቴ. 19፡17፤ ማር. 10፡17-18፤ መዝ. 16፡2።

መ. የሕይወት ዛፍ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ እንዲሆን ያደርገዋል (ዮሐ. 15፡5)፣ የእውቀት ዛፍ ግን ሰው በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምጽና ከእርሱ ኢ-ጥገኛ እንዲሆን ያደርገዋል (ተዛ. ዘፍ. 3፡5)፦

1. መብላት ጥገኝነትን ያሳያል፤ በሕይወት ዛፍ በምሳሌ እንደታየው እግዚአብሔር ምግባችን መሆኑ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለማቋረጥ ጥገኞች መሆን አለብን ማለት ነው።
2. የእውቀት ዛፍ ኢ-ጥገኝነትን ያሳያል፤ በእግዚአብሔር ዓይን፣ የሰው የመጀመሪያውና ታላቁ ኃጢአት ኢ-ጥገኝነት ነው።

ሠ. ሁለቱ ዛፎች በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚሄዱና በራእይ መጽሐፍ የሚጠናቀቁ ሁለት መስመሮችን፣ ሁለት መንገዶችን—የሕይወትን መንገድና የሞትን መንገድ—ያመጣሉ፦

1. ሞት የጀመረው ከእውቀት ዛፍ ነው (ዘፍ. 2፡7)፣ የሚጠናቀቀውም በእሳት ባሕር ነው (ራእ. 20፡10፣ 14)።

2. ሕይወት የጀመረው በሕይወት ዛፍ ነው፣ የሚጠናቀቀውም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ በሕይወት ውኃ ከተማ ነው—22፡1-2።

**II. በሕይወት ለሆነው ለእግዚአብሔር ግንባታ በሕይወት እድገታችን ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ በመደሰት በሕይወት መንገድ ውስጥ፣ በሕይወት መስመር ውስጥ፣ ሕይወትን ጠብቆ በማስቀጠል ውስጥ መቆየት አለብን—ዮሐ. 10፡10፤ ራእ. 22፡1-2፤ ኤፌ. 4፡16፤ 2፡21-22፤ ቆላ. 2፡19፦**

*ሀ.* በሕይወት *መንገድ* ላይ የምንቆየው በትክክልና ስህተት *መርህ* ሳይሆን በሕይወት *መርህ መሠረት* በመኖርና በ*መሥራት* ነው፦

1. በትክክልና ስህተት *መሠረት* ሳይሆን በ*መንፈሳችን* ውስጥ ባለው የሕይወት ስሜት፣ በሕይወት ምሪት *መሠረት መኖርና መሥራት* አለብን—ሮሜ 8፡6፤ 2ቆሮ. 2፡13።
2. የክርስቲያን ኑሮ *መስፈርቱ* በውስጣችን የሚያድረው ክርስቶስ በእኛ ውስጥ *መገኘቱ* ነው፤ ትክክል ነው ወይስ ስህተት የሚል ጥያቄ ሳይሆን፣ በውስጣችን ያለው *መለኮታዊ* ሕይወት ከነገሩ *ጋር* የ*መስማማቱ* ወይም ያለ*መስማማቱ* ጥያቄ ነው—*ማቴ*. 17፡3፣ 5፣ 8፤ ተዛ. 2፡15-16።

*ለ.* በሕይወት *መንገድ* ላይ የምንቆየው ጌታን ፈጽ*መን* በ*መውደድ*፣ ከእርሱ በኃላ እንዲሮጡ ሌሎችን በ*መሳብ* ነው—*ማር*. 12፡30፤ *መኃ*. 1፡4፦

1. ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ ለ*መደሰት*፣ ሁልጊዜ "ጌታ ኢየሱስ፣ እወድሃለሁ" ብለን ለእርሱ *መንገር* አለብን፤ ለጌታ ኢየሱስ የሚቃጠል ፍቅር ካለን፣ በሁሉ ነገሮች የ*መጀመሪያውን* ስፍራ ከሰጠነው፣ እርሱ የሆነውን ነገር በሙሉ እንደሰታለን—ራእ. 2፡4-5፣ 7።
2. ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ ለ*መደሰት*፣ የጌታ ኢየሱስን ውድ *ማንነት* በእውነት ወደ *ማድነቅ*፣ ወደ *መውደድ* እና ወደ *መደሰት* ሰዎችን በ*ማምጣት* ለእርሱ እነርሱን *ማጨት* አለብን—2 ቆሮ. 11፡2-3።

*ሐ.* በሕይወት *መንገድ* ላይ የምንቆየው ቃሉን እየጸለዩ-በ*ማንበብ*፣ ቃሉን በ*ማሰላሰል* እና የእምነት *መንፈሳችንን* በ*ማንቀሳቀስ* ቃሉን ወደ ሌሎች በ*ማገልገል* በኩል ኢየሱስን በሙ*ብላት* ነው—ዮሐ. 6፡57፣ 63፤ ኤር. 15፡16፤ *መዝ*. 119፡15፤ *ማቴ*. 4፡4፤ 24፡45፤ 1 ቆሮ. 2፡4-5፣ 13፡

1. የእያንዳንዱ ቀን አዲስ ጅ*ማሬ* እንዲኖረን በ*ማለዳ* እርሱን በቃሉ *መደሰት* አለብን፣ በብዙ እና ጥንቃቄ በተሞላበት *ማሰላሰልም* ቃሉን *መቀበል* አለብን—*መዝ*. 119፡15፣ 147- 148፤ ተዛ. ሌዋ. 11፡3።
2. በየዕለቱ በጊዜውም አለጊዜውም ክርስቶስን ለሁሉም አይነት ሰዎች *መናገር* አለብን (ሐዋ. 5፡42፤ 8፡4፤ 2 ጢሞ. 4፡2) በ*ማንኛውም* ዓይነት ስብሰባ ላይም የ*መናገር* ል*ማድን* ለ*መገንባት መትጋት* አለብን (1 ቆሮ. 14፡26፣ 4-5፣ 12፣ 31)።

*መ.* በሕይወት *መንገድ* ላይ የምንቆየው ከሕይወት *መንፈስ* ሕግ *መለኮታዊ* አቅም *ጋር* ሦስታንዱን አምላክ እንደ የሕይወት *መንፈስ* ሕግ በ*መደሰት* ነው—ሮሜ 8፡2፤ ኤር. 32፡39፦

1. በኤደን ገነት ውስጥ በሁለቱ ዛፎች ሕይወትን፣ *መልካምን* እና ክፉን እናያለን፤ የሕይወት *መንፈስ* ሕግ በ*መንፈሳችን*፣ *መልካምን* የ*ማድረግ* ሕግ በተፈጥሮአዊው፣ ኢ-ጥገኛ አእምሮአችን እና  ክፉን የ*ማድረግ* ሕግ በሥጋችን ያለን ትንሺ ኤደን ገነት ነን—ሮሜ 7፡23፤ 8፡2፣ 16።
2. ለሦስታንዱ አምላክ ወደ ሦስቱ ክፍላችን እንደ ሕይወት *መታደል*፣ በ*መንፈስ መሠረት* በ*መመላለስ* እና አእምሮአችንን በ*መንፈሳችን* ላይ በ*ማድረግ* የሕይወት *መንፈስ* ሕግን "*ማብራት*" አለብን—ቁ. 2፣ 4፣ 6፣ 10-11።

*ሠ.* በሕይወት *መንገድ* ላይ የምንቆየው በትንሣኤ፣ እንደ ትንሣኤው ሕይወት ዛፍ በወርቃ*ማው መቅረዝ* በተ*መለከተው* እንደ ክርስቶስ አካል በቤተ ክርስቲያን እውነታ ውስጥ በ*መኖር* ነው፤ ይህም የሕይወት ከተ*ማ* እንደሆነችው እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር *መገለጥ* የእግዚአብሔርን ክብር እንድንሸከም ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ ዘጸ. 25፡31-40፤ ራእ. 1፡11-12፤ 21፤ 10-11።

**III. የክርስቶስን ድል ለማሳየት ወንዱን-ልጅ ለመሆን እና ለክርስቶስ እርካታ ሙሽራይቱ ለመሆን በሕይወት መለወጥ እንችል ዘንድ ድል ነሺዎች የምንሆንበት ልዩና ብቸኛው መንገድ ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ በመብላት እና በመደሰት ነው—2፡7፣ 17፤ 3፡20-221፤ 12፡5-12፤ 19፡7-9፤ 22፡2፣ 14።**

*© 2022 Living Stream Ministry*